Amharisch

# የእግዚአብሔር ሰው መሆን ለእኛ ለሰው ልጆች

ከብጹእ ጳጳስ አቡነ

በ2025 ዓ.ም. የጾምና የንሰሃ ጊዜ

(ዶክተር) ጌኦርግ ቤትሲንግ የተላለፈ ሓዋርያዊ ደብዳቤ

## “የመረጥኩት ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት” (ሉቃስ 9፣35)

በጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እምነት ያልችሁ ውድ ወንድሞች እና እህቶች ! ሥር መሰረታቸውን የሚያውቁ ማደግ እና ፈተናዎችን ሁሉ ማሸነፍ ይችላሉ። ይህ አባባል ለሕይወትም ለእምነትም ይሠራል።

በዚህ ሓዋርያዊ ደብዳቤ፣ የሁላችሁም ትኩረት በእምነት መግለጫ በሆነው፣ መሰረታዊ ባህሪያቱ በትክክል ከ1,700 ዓመታት በፊት በተቀናበረው እና ከጥቂት አሥርት ዓመታት በኋላ ደግሞ፣ እንደ “ታላቅ የሃይማኖት መግለጫ” ተደርጎ በተወሰደው ጸሎተ ሃይማኖት ላይ እንዲሆን እወዳለሁ። ይህ የእምነት መግለጫ ለቤተክርስቲያን እንዲሁም በዉስጧ ላሉ አማኞች ሁሉ በጊዜ ሂደት ለሚያደርጉት ጉዞ ጠንካራ መሰረት ይሰጣል።

ይህ ጽሑፉ በጎተስሎብ (Gotteslob) ገጽ (586.2) በጀርመን እና በላቲን ቋንቋ ተጽፎ ይገኛል። የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ በመጀመሪያ የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ነው እና ይህም ከመነሻው ጋር የተያያዘ ነው።

## ከኮንስታንቲኖፕል ጉባዔ በኋላ ስለአንድነት የተደረገ ትግል

ታላቁ ቆስጠንጢኖስ የመጀመሪያው የሮም ንጉሠ ነገሥት ከክርስቲያኖች ጋር በግልጽ ከጎናቸው በመቆም በክርስቲያኖች ላይ ይደርስ የነበረውን የረዥም ጊዜ ስደት በሚላኖ ስምምነት በ313 ዓ.ም. ከጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ እንዲቆም አደረገ።

ይህ ታላቅ ንጉሰ ነገስት በዚህ ብቻ ሳይገደብ ቤተክርስቲያንን በገንዘብ መዋጮ ማገዝ ብቻም ሳይሆን እሱ ራሱ የክርስትና እምነትን በመቀበል በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የጵጳሳትን ሚና በከፍተኛ ሁኔት አጠንክሯል።

በእርግጥ የእሱ ዓላማ ሃይማኖታዊ ብቻ አልነበረም። በፖለቲካዊ መልኩ የሮማን ኢምፓየር አንድነት በቤተክርስቲያን አንድነት በኩል መደገፍ ስለፈለገም ጭምር ነው። ነገር ግን ይህ አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ አለመግባባትና ስጋት ፈጥሯል። በመሆኑም በ318 ዓ.ም. ከክርስቶስ ልደት በኋላ በግብጽ አሌክሳንድሪያ እንደ ሰደድ እሳት የማያባራ ግጭት ተነሳ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ አርዮስ የሚባል ካህን የእግዚአብሔርን ብቸኛ አምላክነትና ወደር የለሽነት ለመጠበቅ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ክዷል፣ ይህም አስተሳሰብ በአንድ ወገን የእስራኤል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በሌላ በኩል ደግሞ የግሪክ ፍልስፍና ትሩፋት ነው። ስለዚህ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከአብ ጋር ከዘላለም ጀምሮ ሳይፈጠር የኖረ ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ዓለምን ለመፍጠርና

ከሰዎች ጋር ላለው ግንኙነት የሚያሳልጥ የመጀመሪያውና ፍጹም ፍጡር እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሆነ አምላክ አልነበረም ይላል።
አርዮስ እና ተከታዮቹ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ያላቸው እአዲሁም በፍልስፍና ከፍተኛ እውቀት የነበራቸው ስለነበሩ ትምህርቶቻቸውን በጊዜው ከነበረው የእውቀት ደረጃ ጋር ለማስማማት ጥረት አድርገዋል። ይህ የእግዚአብሔር ሰው መሆን አመለካከት ለነሱ ከእውቀት ወይም ከትክክለኛ አመለካከት ማነስ የመጣ አድርገው ይወስዱታል።
በዘመኑ ብዙ የተማሩ የሚባሉት ይህንን የአሪዮስን አመለካከት ተጋሩ። አርዮስ በኤጲስ ቆጶሱ አማካይነት የጋራ የሆነውን የክርስትና እምነት መሠረት አጥብቆ እንዲጠብቅ ከተጠየቀም በኋላም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ግጭቱ ይበልጥ እየተባባሰ ሄደ።

ንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ነገሩ በጣም ስላሳሰበውና ውዝግቡን ለመፍታት የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ ሲኖዶስ ለማዘጋጀት ተነሳሽነቱን ወሰደ። በ325 ከክ.ል.በኋላ በክረምቱ መጀመሪያ ላይ፣ ወደ 250 የሚጠጉ ተሳታፊዎች በኒቂያ ከነበረው የንጉሠ ነገሥቱ መኖሪያ ብዙም ሳይርቅ ተሰበሰቡ፣ እሱም የዛሬው ኢዝኒክ በቱርክ የቡርሳ ግዛት የሚገኘው ቦታ ነው።
ይህ ዓለም አቀፍ ጉባዔ የተከፈተው የሮም ንጉሠ ነገሥት እና የርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወኪሎች በተገኙበት ሲሆን ከፍተኛ ውይይት ከተደረገ በኋላ የአርዮስን እና የተከታዮቹን አቋም አውግዞ ጉባዔው የራሱን አዲስ መመሪያ በእምነት መግለጫ መልክ አጸደቀ።

## እኛ ስለ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ የምናምነው ነገር

የዚህ ቃል ማዕከላዊ ነጥብ ወይም አስኳል ልጅ የሆነው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ራሱ የአብ ማንነት ነው የሚለው ነው። አምላክ ከአምላክ - ብርሃን ከብርሃን - እውነተኛ አምላክ - ከእውነተኛ አምላክ - የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ከአብ ጋር በሁሉ ነገር ትክክል የሆነ ነው።
ስለ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰብዊነት “consubstantial” የመጨረሻው ቀመር ወይም አገላለጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ አልተገኘም ነገር ግን የግሪክን ፍልስፍና ቋንቋ እና አስተሳሰብ ተጠቅሞ ስለ እግዚአብሔር ልጅ የሚናገረውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አነጋገር እውነታን የማይገልጽ ተራ ምሳሌያዊ
ዓረፍተ ነገር ተደርጎ እንዳይወሰድ ለመከላከል ነው.
ከኒቂያ ጉባኤ ውሳኔዎች በኋላ “አሪያኒዝም” እየተባለ በሚጠራው ጉዳይ ላይ የተፈጠረው አለመግባባት ለረጅም ጊዜ መባባሱን የቀጠለ ቢሆንም፣ የመጀመሪያው ሲኖዶስ የወሰነው ውሳኔ ውሎ አድሮ የሁሉም የክርስቲያን ቤተ እምነቶች እምነት ሥልጣን ያለው በመሆኑ ትልቅ የጋራ መሠረት ሆኖ ቆይቷል።

## ወደ ጥንት ጠዋቱ መነሻ ወደ ክርስቶስ መመለስ

በኄ.እ.ክ. እምነት የተከበራችሁ ወንድሞችና እህቶች፣ እስከዚህ ነጥብ ድረስ ቀልባችሁን ለመሳብ ከተሳካልኝ፣ ከዛሬ 1,700 ዓመታት በፊት የተከሰተ ክስተትን ዛሬ ማስተናገድ ለምን አስፈለገን የሚለውን ጥያቄ በውስጣችሁ እንደሚመላለስ ተስፋ አደርጋለሁ።

ከታሪካዊ ፍላጎት ባለፈ በዚያን ጊዜ የተከናወኑት ክንውኖችና ውሳኔዎች በዛሬው ጊዜ ላሉ ክርስቲያኖች ትርጉም የላቸውምን? አዎ እነሱ ያሉት በቀላሉ እኛ አማኞች የምንኖረው ከመነሻው ስለሆነ እና የመነሻው እውቀት እራሳችንን በደንብ እንድናውቅ ስለሚረዳን ብቻ ነው።

በእምነቴ ውስጥ በትጋት መሳተፍ እና ስለ ቅድስት ሥላሴ - ስለ ቤተ ክርስቲያን - ስለ ደህንነት እና ስለ ይቅርታ - ድርብ ትዕዛዝ ስለሆነው ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ባልንጀራ ፍቅር - ስለ ጸሎት እና ምስጢራት - ስለ ተስፋው የዘላለም ሕይወት ታላቅ አመለካከት ያሉትን መግለጫዎች በጥልቀት ማግኘቴ በግሌ የሚያበለጽግ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በስተመጨረሻ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ስለ እርሱ የምናምነው እምነት ስንመጣ፣ ይህ የክርስትና እምነት ማዕከላዊ አስኳል ሆኖ እናገኘዋለን።

## የንቂያ ጉባዔ በምን መልኩ የዛሬን የክርስትና ሕይወት ይቀርጻል

በነገራችን ላይ የኒቂያ ጉባዔ ብቸኛው አስገዳጅ ውሳኔ ዓመታዊው የፋሲካ ክብረ በዓል በጸደይ የመጀመሪያ ሙሉ ጨረቃ በሚወጣበት እሑድ ቀን እንዲከበር ብቻ አልነበረም - በእርግጥ አሁንም በዚህ የቀን መቁጠሪያ ቀን ተጠቅመን ፋሲካን ክብረ በዓል እናከብራለን። እንደ እግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ሆኖ በዚህ ዓመት የፋሲካን ክብረ በዓል ከኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ጋር በጋራ እናከብራለን።

በዚህ የክርስቲያናዊ የጋራ ምክር ቤት የተቋቋመበትን አንደኛ ዓመት በምናከብርበት ወቅት፣ በተመሳሳይ ቀን ሁሉም ክርስቲያኖች የጋራ የትንሳኤ በዓል የሚያከብሩበትን ሁኔታ የሚያበረታቱ አዳዲስ ተነሳሽነቶችን ለመደገፍ ፍላጎት እንዳለን ለመግለጽ እንወዳለን።

አብዛኛው ሰው እንደሚቀበለው የንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ የገና በዓል በታኅሣሥ 25 ቀን እንዲከበር የወሰነው ውሳኔ ከኒቂያ ጉባኤ ጋር የተያያዘ ነው እናም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እውነተኛ አምላክ እና እውነተኛ ሰው መመስከሩን እንደ መግለጫ እና "ውጫዊ በዓል" መረዳት ይቻላል።

## በክርስቶስ ያለን እምነት አሁን ባለንበት ጊዜ

እ.ኤ.አ. በ2023 የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው የቤተክርስቲያንኒቱ ኣባላት በተከታዮቹ ጉዳዮች ላይ የሰጡት ሃሳብ እኔን በጣም አሳስቦኛል፡-
"ራሱን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገለጠ አምላክ እንዳለ አምናለሁ" የሚለው አመለካከት ከዚህ ቀደም ከተሰሩት ጥናቶች አኳያ ሲነጻጸር በእጅጉ ቀንሷል። ዛሬ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል 32 በመቶ (32%) የሚሆኑት በዚህ አባባል ይስማማሉ።
አንድ ሰው ይህ በአጠቃላይ እየጨመረ የመጣው የዓለማዊ አስተሳሰብ እድገቶች ውጤት እንደሆነ ሊቆጥረው ይችላል በዚህም የእግዚአብሔር ሕልውና ለብዙ እና ለብዙ ሰዎች ትርጉም የለሽ ሆኗል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ግላዊ ፅንሰ-ሀሳብ ትነት በግልጽ ከማዕከላዊ ክርስቲያናዊ እምነቶች መቀንጨር ጋር አብሮ ይመጣል።
እያንዳንዱ የክርስቲያን ትውልድ በእርግጥም እያንዳንዳችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ማን ነበር? ኢየሱስ ማነው? አርአያ - ነቢይ - የናዝሬቱ ረቢ (አስተማሪ) - በዓለም ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሰው ለሚሉት መልስ መስጠት መቻል አለብን፡- ፡- እነዚህ እና ሌሎች ተመሳሳይ መግለጫዎች ከቤተክርስቲያን ወሰን ባሻገር በታላቅ ርህራሄ ማስተጋባት መቀጠላቸውን ጥናቶች ደጋግመው ያረጋግጣሉ።
ነገር ግን አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በሕይወት ዘመኑ መኖር እንዲችል እና በእርሱ በማመን በጥሩ ሁኔታ ለመኖር እና ለመሞት ይህ በቂ ነውን?

## ዓለም ሳይፈጠር በፊት ከአብ ዘንድ ለእኛ ለሰዎች ደህንነት የተወለደ

በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክርስትና ሕይወት ከነበሩት ታላላቅ የቤተክርስቲያን ነገረ መለኮት ሊቃውንትና ጳጳሳት መካከል የአሌክሳንደሪያው ቅዱስ አትናቴዎስ አንዱ ነው። ይህ ቅዱስ ስለ ንቂያ የሃይማኖት አንቀጽ በተመለከተ ሁለት ጊዜ ከግብጽ አንስቶ እስከ ዓለም ጥግ እስከ ትሪየር ለመሰደድ የተዘጋጀ ነበር።

በእምነቱ ጸንቶ የኒቂያ ውሳኔ ያስፈለገበትን ሦስት ተጨማሪ ምክንያቶች ተናግሯል፡- ክርስቶስ ወልድ አምላክ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር አምላክን ለእኛ ለሰው ልጆች ሊገልጥልን አይችልም ነበር። እርሱ በአማላጆች እና በነቢያት መስመር ውስጥ አንድና ብቸኛ ይሆናል። ስለ እግዚአብሔር የሆነ ነገር መናገር ይችላል ነገር ግን  እርሱ ራሱ እግዚአብሔር አይደለም።

እግዚአብሔር ራሱ ሰው ባይሆን ኖሮ በሕይወት የእግዚአብሔር መንግሥት አዋጅ የኢየሱስ መከራ ሞትና ትንሣኤ በቤዛና ነፃ በሚያወጣ መንገድ ለሰዎች ሁሉ መዳን በእውነት ምንም ሊለወጥ ባልቻለ ነበር።በአዲሱ እና በእውነተኛ ውስጣዊ ነፃነት እና ከእግዚአብሄር ጋር ከሀጢያት እና ከበደለኛነት ሊፈወስ በሚችል አዲስ ግንኙነት ባናምንና ባንቀበል ኖሮ በእምነታችን የተሳሳተ መንገድ ላይ እንሆን ነበር።

በመጨረሻም የቤተክርስቲያን አባት አትናቴዎስ እንዲህ የሚል ሓሳብ አንስቷል፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ብቻ ሳይሆን በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ካልሆነ ወደ እርሱ

መጸለይ መንበርከክና ማምለክ ጣዖት አምልኮ ይሆን ነበር ብሏል።

ከኢየሱስ ጋር ያለው ግላዊ ውይይት እና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ጸሎት የሚያነጻ እና የሚያበረታታ ሥነ ልቦናዊ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል፣ ነገር ግን ከዚያ ውጭ በእኛ ሰዎች እና በህይወታችን መነሻ መሰረት እና ግብ በሆነ በእግዚአብሔር መካከል እውነተኛ ግንኙነት ሊፈጥሩ አይችሉም።
እኔም በግሌ እነዚህን ከበድ እና ጠለቅ ያሉ ሓሳቦች በጣም አሳማኝ ሆኖ አግኝቻቸዋለሁ።

## አብሮ የመዳዝ ባሕልና የህብረ - ክርስቲያናዊ ምስክርነት

በጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ከነበረው ስለ አዳኛችን እየሱስ ክርስቶስ አመጣጥና ባህሪ ከመመርመር በበለጠ የንቂያን ጉባዔ ስለዚህም ሆነ ስለሌሎች ሃሳቦች ማመሳከሩ ተገቢ ነው።

ይህ እጅግ ጠቃሚ ክስተት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሂደት ውስጥ በጣም መሰረታዊና ተደጋጋሚ ሃይማኖታዊ ክርክሮች መሰረታዊ የእምነትና የሥነ ምግባር ጥያቄዎች፣ አሁን ካለችው ቤተክርስቲያን በበለጠ ሁኔታ ይነሳ እንደነበር ይታወቃል። ስለዚህ ግጭቶችና ውይይቶች ሁሌም አብረውን አሉ። ዛሬም ቢሆን እነዚህ ሁኔታዎች አብረዉን አሉ በመሆኑም እኛም በልበሙሉነት ቤተክርስቲያን አስቀድማ ያዳበረችውን ሲኖዶሳዊ ባህልና መዋቅር ችግሮችን ለማርገብ እንድትጠቀምበት እንጠይቃለን። በዚህም ሁኔታ እምነት ይበልጥ እየጎለበተና እየዳበረ ይሄዳል የቤተክርስቲያንም አንድነት ይጠበቃል ይታነጻልም።

ከ 2021-2024 በተደረገው ዓለም አቀፍ ሲኖዶስ ላይ ሲኖዳሊቲ ወይም የሕብረት ጉዞ በሚለው ርዕስ ላይ የተገኘው ውጤት አሁን ላይ በሁሉም ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን እርከኖች ላይ በተጠናከረ መልኩ መተግበር ያለበት ጥንታዊና መልካም ባሕል ነው። በጊዜው የነበረው የሮማ ንጉሰነገስት ትልቁ አመለካከት ቤተክርስቲያን በጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ላይ ባላት እምነት እንዳትከፋፈል ነው እንዲሁም ይህንን ሁኔታ በቤተክርስቲያን ላይ መጠበቅ መሰረታዊ በሚባል ደርጃ ትምክህተኝነት አይደለም።

አንድነት በብዙ ሰዎች እይታ ዘንድ ወሳኝ ክርስቲያናዊ ምስክር ሆኖ ይኖራል። በዮሐንስ ወንጌል (17፤21) ላይ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንደጸለየው „ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ, [...] በዚህም አኳሃን ዓለም ያምናል። እኔ በግሌ ከብዙ ከማህበራዊ ቡድኖች እና ከፖለቲካዊ ውሳኔ ሰጪዎች ጋር በሚደረጉ ውይይቶች ይህ ነገር ብዙ ጊዜ አጋጥሞኛል።

ምንም እንኳን በግላቸው ባያምኑም እኛ ክርስቲያኖች፣ በኢየሱስ መንፈስ፣ በሁሉም ሃይማኖታዊ ተቋሞች በዓለም ላይ ላለው ፍትህ፣ ለሰው ልጆች አንድነት በመሠረታዊ እሴቶች እና አመለካከቶች ላይ እንደምንሠራ ያምናሉ። ለዚህም ነው የጋራ የሃይማኖቶች ወይንም ኢኩሜኒካል ጥረት ለበለጠ የጋራነት እና ለሚታየው አንድነት በጣም አስፈላጊ የሚሆነው።

## የእምነት ውበትና ውስጣዊ ትስስር

በጌ.እ.ክ. እምነት ያላችሁ ውድ ወንድሞች እና እህቶች በክርስትና እምነት ውስጥ ስላላችሁ ተነሳሽነትና በጊዜአችን ባለችው ቤተክርስቲያን በተናጠል ስለምትሰጡት አገልግሎትና ምስክርነት በጣም አድርጌ ላመስግናችሁ እወዳለሁ። አሁን በምንገኝበት በኢዩቤልዩ ዓመት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላችሁን እምነት በግል እና በህብረት እንድታስተነትኑበት ላበረታታችሁ እወዳለሁ።
ለእናንተ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴት የእምነት መገለጫስ ከሕይወታችሁ ጋር በተያያዘና አግባብነት ባለው መልኩ ውጤታማ ያደርጋችኋል? በምትጸልዩበት ጊዜስ ከጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ጋር ምን ብላችሁ ትነጋገራላችሁ? እኔ ይህንን የእምነት መገለጫ በምደግምበት ጊዜ በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ ያለውን ጥልቅ ቅንጅት ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያለውም ውበት መንፈሴን ያረጋጋልኛል።
ይህ ታላቁ የእምነታችን መገለጫ በእርግጥ ለእግዚአብሔር ውዳሴ የምንሰጥበት አንድ መንገድ ነው። ለዚህም ነው አብዛኛውን ጊዜ በንግግር ብቻ ሳይሆን በዝማሬም የምናመሰግነው። ለዚህም ነው የእኛ ሕይወት ያለው እምነታችን በመሰረታዊነት ደረጃ በራሱ አምልኮአችን ነው የምንለው።

ለእናንተና ከእናንተ ጋር ሕብረት ላላቸው ሁሉ የእግዚአብሔር የተትረፈረፈ በረከት እንዲበዛላቸው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እለምናለሁ።

ኣሜን።

ሊምቡርግ 2ኛ የጾም ሰንበት

ብጹእ አቡነ ቤትዚንግ

# ታላቁ ወይንም የንቂያ-ኮንስታንቲኖፕል የእምነት መግለጫ / ጸሎተ - ሃይማኖት

ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።

ከአብ ለዘለዓለም በተወለደ የእግዚአብሔር አንድ ልጅ በሆነ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ፤ እርሱ አመላክ ከአምላክ ብርሃን ከብርሃን፣ እውነተኛ አምላክ ከእውነተኛ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ከአብ ጋር ትክክል የሆነ ነው።

ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጠረ።

ስለእኛ ስለ ሰዎች ስለ ደኅንነታችንም ከሰማይ ወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከድንግል ማርያም ተወለደ፣ ሰውም ሆነ።

በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን ስለኛ ተሰቀለ፤ ሞተ፤ ተቀበረም።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው በሶስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ፤ ወደ ሰማይ ወጣ፣ በአብም ቀኝ ተቀመጠ ሕያዋንና ሙታንን ለመፍረድ ዳግመኛ በክብር ይመጣል፣ መንግሥቱም ማለቂያ የለውም።

በነቢያት አፍ በተናገረው፣ ከአብና ከወልድ በሠረጸው በሕይወት ሰጭ ጌታ በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ።

እርሱን ከአብና ከወልድ ጋር እንስገድለት እናምልከውም።

በአንዲት፣ ቅድስት፣ የሁሉም በሆነች በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን አምናለሁ።

ለኃጢአት ስርየት በተሠራችው በአንዲት ጥምቀት አምናለሁ።

በሙታን ትንሣኤ፣ በሚመጣው የዘለዓለም ሕይወትም ተስፋ አደርጋለሁ።

አሜን።

# የጸሎት ጥሪ


1 ክርስቶስ አምላካዊ ጌታ
ለመውደድ ጥንካሬ ያለው ብቻ ይወድሃል፡-
ጌታ ሆይ አንተን የማያውቁህ ሳይሆኑ
ማን እንደሆንክ የሚያዉቁ ሁሌም ይናፍቁሃል

2 ክርስቶስ አንተ ተስፋዬ
ሰላሜ ፤ ደስታዬ ፤ ሕይወቴ ነህ
ክርስቶስ ሆይ መንፈሴ ለአንተ ይሰግዳል;
ክርስቶስ ሆይ ሁለም ወደ አንተ እጸልያለሁ

3 ክርስቶስ ሆይ ሁሌ አንተን ብቻ
በመላው ሃይሌና መንፈሴ አጥብቄ እይዛለሁ
ክርስቶስ ሆይ አንተን ብቻ ወዳለሁ
አንተን ብቻ ፈልጋለሁ አንተን ብቻም እከተላለሁ




(ክርስቶስ አምላክ የእውነተኛ ሕይወት ፈጣሪ ከሚለው
ከሰሌዳው አልፋኑስ የጸሎት መጽሐፍ/ የዳዊት መዝሙር በ +1085 የተወሰደ)



Übersetzung der Ausgabe:
„GOTTES SOHN – MENSCH FÜR UNS“
HIRTENWORT
zur Österlichen Bußzeit 2025
von Dr. Georg Bätzing, Bischof von Limburg